# የአገልግሎት ቅጣት ሥራ ለተፈረደበት ግለሰብ የሚሆን መረጃ

# የ“ሃቭታሐት ሀክናሳ” መደጐሚያ ባለመብት መሆን

אמה

በ“ቢቱዋሕ ሀሌኡሚ” በማብራሪያና ሕዝባዊ ግንኙነት ክፍል የቀረበ
ጥር 2016 • 323 ה"ח

“ሀቢቱዋሕ ሀሌኡሚ”
በሕይወትዎ ወሳኝ ወቅት ከጐንዎ ነው
*6050• www.btl.gov.il

## የቅጣት አግልግሎት ሥራ ይሠራሉ ወይ? የ“ሃብታሐት ሀክናሳ” መደጎሚያ ባለመብት ስለመሆንዎ ያጣሩ

በቅጣት ሥራ ሕግ መሠረት በሕዝባዊ ሥራ መስክ የአገልግሎት ሥራ ተፈርዶብዎት ከሆነ ምናልባት የ“ሃብታሐት ሀክናሳ” መደጎሚያ ባለመብት ሊሆኑ ይችላሉ።
የድጎማ ባለመብትነት የሚወሰነው በ“ቢቱዋሕ ሀሌኡሚ” አማካይነት ነው።

## ድጎማውን ለማግኘት መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው?

- በተሰጠው ፍርድ መሠረት በሕዝባዊ ሥራ ቦታ ሙሉ ቀን የሚሠሩ ከሆነ።
- ገቢ ከሌለዎት ወይም ያለዎት ገቢ ዝቅተኛ በመሆኑ “ሀሽላማት ሀክናሳ” የሚቀበሉ ከሆነ
- ማመልከቻውን ያቀረቡት የአገልግሎት ሥራውን በሚሠሩበት ጊዜ ከሆነ

## ልብ ያድርጉ፣

የአገልግሎት ሥራ ለተፈረደበት ሰው የ“ሃብታሐት ሀክናሳ” መደጎሚያ ባለመብትነት የሚሰጠው **የቅጣቱን ሥራዎች በሚሠሩበት ወቅት** ነው። ከሥራዎቹ የሚቀሩ ከሆነ የሥራዎቹ መጨረሻ ጊዜ ይራዘማል። እንዲያውቁት፣ ከሥራው በሚቀሩበት ጊዜ መደጎሚያው የሚከፈልዎት ከሥራው የቀሩት በቂ ምክንያት ኖሮዎት ከሆነ ብቻ ነው።

## የትዳር ጓደኛ ካለዎት፣

የትዳር ጓደኛዎም ቢሆኑ የ“ሃብታሐት ሀክናሳ” ባለመብት የሚያደርጋቸውን ግዴታዎች በሙሉ ማሟላት አለባት። የገቢ መመዘኛዎችን ማሟላት፣ እንደዚሁም ለባለመብትነት ምክንያት ት ያስፈልጋል። ለምሳሌ ያህል በ“ሸሩት ታዓሱካ” ሥር ሥራ የምትፈልግ፣ በዝቅተኛ ደመወዝ የምትሠራ ወይም እስከ 2 ዓመት ዕድሜ ያለው ልጅ ያላት ወይም መሥራት የማትችል መሆን አለባት።

ለእርስዎ፣ ለትዳር አጋርዎ ወይም ለልጅዎ መኪና ያላችሁ ከሆነ የባለመደጎሚያ ባለመብት ሊሆኑ የሚችሉት የመኪናው ዋጋ ከ40,760 ሼቄል የማይበልጥ ከሆነ ነው። ለሕክምና አገልግሎት የሚያገለግል መኪና ካላችሁ ለድጎማው ባለመብት የምትሆኑት በልዩ ሆኔታዎች ነው።

## የድጎማው ማመልከቻ አቀራረብ ሁኔታ

ድጎማውን ለመቀበል በቅርብዎ ለሚገኝ የ“ቢቱዋሕ ሀሌኡሚ” ቢሮ ለ“ሃብታሐት ሀክናሳ” (5619/בל) የተሰኘ ማመልከቻ እንዲያቀርቡ ያስፈልጋል።

ማመልከቻውን **የአገልግሎት ሥራውን በጀመሩበት ወር** ላይ ማቅረቡ ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ባለመብትነት የሚጀመረው ማመልከቻውን ካቀረቡ ከአንድ ከወር በኋላ ስለሆነ ነው።

**ያስተውሉ፣ የአገልግሎት ሥራ የሚያበረክቱ ከሆነ የቅጣት ሥራውን ከጨረሱ በኋላ ማመልከቻ ቢያቀርቡ የድጎማው ባለመብት አይሆኑም።**

የማመልከቻውን ቅጽ ከ“ቢቱዋሕ ሀሌኡሚ” የቅጾች ክፍል ድረ ገጽ ላይ ሊያወርዱ ይችላሉ።

ማመልከቻውን ለማቅረብ በቅጹ ላይ የተጠየቁትን ማስረጃዎች በሙሉ ማቅረብ ይኖርብዎታል። ከእነሱም ውስጥ በማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የቅጣት ሥራዎች ተቆጣጣሪ ዘንድ የአገልግሎት ሥራ ፈቃድ ማምጣት ያስፈልጋል።

## የመደጎሚያው ክፍያ መቀጠል

የአገልግሎት ሥራውን ከጨረሱ በኋላ ለድጎማው ባለመብት ሊሆኑ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው መሥራት ካልጀመሩ ወይም መሥራት ቢጀምሩም ደመወዝዎ ዝቅተኛ ከሆነ ነው። በዚህ ሁኔታ የ“ሃብታሐት ሀክናሳ” ድጎማ ባለመብት ለመሆን ወደ “ሼሩት ታዓሱካ” መሥሪያ ቤት የሚላኩ ሲሆን ለጤና ሁኔታዎና ለአካላዊ ብቃትዎ የሚስማማ ማንኛውንም ዓይነት ሥራ መሥራት አለብዎት።

### ሌላ ተጨማሪ ነገሮች ማወቅ ይፈልጋሉ?

ለ“ሃብታሐት ሀክናሳ” ድጎማ ባለመብት የሚያደርጉ ሁኔታዎች ዝርዝር መረጃና ስለሚከፈለው ገንዘብ መጠን

WWW.BTL.GOV.IL

ከሚባለው ከ“ቢቱዋሕ ሌኡሚ” ድረ ገጽ ላይ /קצבאות הבטחת הכנסה ከተሰኘው ክፍል ሊያገኙ ይችላሉ። እንደዚሁም ከማኛኛውም ቅርንጫፍ ሊቀበሉ ከሚችሉት የማብራሪያ ወረቀት ላይ ሊያገኙ ይችላሉ።

ማንኛውም በተባእታይ ጾታ የተጻፈው አንስታይ ጾታንም ይመለከታል።